# የእውነታ ሉህ ቁ. ፱

# የዘር ልዩነት ድህነት በመኖሪያ ቤት ማግኘትና ማጣት ላይ ያለው ተጽእኖ

## በዘር ልዩነት የተፈረጁ ሰዎች በመኖሪያ ቤት ማግኘትና ማጣት ምክንያት ምንኛ ተጎድተዋል?

**በቂ ያልሆነ መኖሪያ ቤት፡** በካናዳ የሚኖሩ ከ50% በላይ የሚሆኑ የቀለም ቤተሰቦች ዓቅማቸው በማይፈቅደው መኖሪያ ቤት (ወደ ቤት እጦት የሚያመራ)፣ እንዲሁም በቂ ባልሆነ (ጥገና ወይም መታደስ የሚያስፈልገው) እና በማያመች (ከሌሎች ችግሮች በተጨማሪ መጨናነቅ የበዛበት) ቤት ይኖራሉ፡፡
ይህም ከ28% በላይ የሚሆኑ በዘር የማይለዩ ቤተሰቦች ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ ይታያል፡፡



**ትልቅ ቤተሰብ ላላቸው ባለቀለም ሰዎች
እና አዳዲስ መጤዎች ዓቅምን የሚመጥን፣
- ሁሉን "አካታች የሆነ ዞን ውስጥ" መኖሪያ ቤት እየተሠራ አይደለም፡፡
እንዲያውም አሁን በደካማ የክልል ህጎች የተነሣ እየተሻረ ይገኛል፡፡**

**ከመጠን በላይ ውክልና (ብዛት)፡** በኦንታሪዮ ውስጥ በቅድሚያ ትላልቅ የከተማ ማዕከላት ለስደተኞች እና ለአዳዲስ ሰፋሪዎች መዳረሻዎች እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ጥራት በሌላቸው ቤቶች በብዛት ለሚኖሩት ለባል ቀለም ማኅበረሰቦች ተመራጭ ቤቶች ናቸው፡፡
**የመኖሪያ ቤት ወጪ**: አብዛኛዎቹ ስደተኞች ከገቢያቸው ከ50% በላይ በመኖሪያ ቤት ጉዳይ እንደሚያጠፉ15 በመቶ የሚሆኑቱ ደግሞ ከገቢያቸው 75% በመኖሪያ ቤት እንደሚያጠፉ አንድ ጥናት አመልክቷል፡፡

**አድልዎ**: ነባር የአገሬው ተወላጅ ሕዝቦች፣ ባለ ቀለም ሰዎች እና ስደተኛ ሰዎች ከመጥፎ መኖሪያ ቤት ሁኔታ በተጨማሪ የገቢ ምንጭን፣ የብድር ታሪክን፣ ዋስ እና ምስክሮች የማግኘት ተደራሽነትን፣ የዘር ማንነትን፣ የኢሚግሬሽን ሁኔታን፣ ጾታን እና እድሜን መሠረት ያደረገ አድልዎ ያጋጥማቸዋል፡፡
**መጤ ኗሪዎች፡** በቅርቡ የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው 80% ስደተኞች የሚኖሩት በኪራይ ቤቶች ነው፡፡
ስደተኛ ሴቶች አስተማማኝ የሆነ መኖሪያ ቤት ባለማግኘት ለከፍተኛ አደጋ ይጋለጣሉ፡፡ 50% የሚሆኑት በቅርብ ጊዜ የመጡ፣ ብቸኛ ወላጆች የሆኑ ስደተኛ ሴቶች፣ በዋናነት መኖሪያ ቤት ፍለጋ ላይ ናቸው፡፡

**ስደተኞች**: ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ስደተኞች እና ጥገኝነት ፈላጊዎች በተወሰነ ጊዜ መጠለያ ውስጥ ይቆያሉ፣ ይህም እንደነዚህ የመሳሰሉ ቡድኖች በከፍተኛ የመኖሪያ ቤት እጦት መሆናቸውን ያሳያል፡፡

## ነባር የአገሬው ተወላጆች ትኩረት

እ.ኤ.አ. በ2011 በቀዳሚ ኗሪ ሕዝቦች (First Nations) ያሉ የመኖሪያ ቤቶች ላይ የተደረገ የፌደራል ግምገማ እንዳመለከተው በህግ በተከለለ አካባቢ ከሚገኙት ቤተሰቦች 41.5% በመቶ የሚሆኑት ቤተሰቦች፣ የአገሬው ተወላጅ ካልሆኑ 7% ብቻ ቤተሰቦች ጋር ሲነፃፀር መኖሪያቸው ዋና እድሳት ያስፈልገዋል፡፡
ከችግሮቹ ውስጥ ሻጋታ ፣ የባክቴሪያ ማመንጫነት ፣ በቂ ያልሆነ ማሞቂያ እና የተበከለ ውሃ የመሳሰሉት ናቸው፡፡
እ.ኤ.አ. በ2016 በኦንታሪዮ ውስጥ በአታዋፒስካት የሚኖሩ ቀዳሚ ህዝቦች (First Nation) 2,100 የሚያህሉ ሲሆን ነገር ግን 340 ቤቶች ብቻ እንደነበሩ ቶሮንቶ ስታር ጋዜጣ ዘግቧል፡፡ ይህም ማለት በአንድ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰቦች ብዙውን ጊዜ ይኖራሉ ማለት ነው፤ አንዳንድ ቤቶች እስከ 13 ሰዎችን ይይዛሉ፡፡
28-34% የሚሆኑት የመጠለያ ኗሪዎች የአገሬው ተወላጅ ናቸው፡፡
በካናዳ ውስጥ በሁሉም የከተማ ማዕከላት ዘንድ መኖሪያ-አልባ ከሆኑት ሰዎች መካከል የአገሬው ተወላጅ ሰዎች ብዙዉን ቁጥር ይይዛሉ፡፡

በብሔራዊ ዘገባ መሠረት፣ የአገሬው ተወላጅ ካልሆኑት (8%) ጋር ሲነጻጸሩ የአገሬው ተወላጅ ነኝ ብለው ማንነታቸውን ሪፖርት ያደረጉ ሰዎች (18%) ማለትም ሁለት ጊዜ እጥፍ የሚሆኑ ስዉር የቤት እጦት ችግር እንደሚያጥማቸው ታውቋል፡፡

**ስዉር የመኖሪያ ቤት እጦት፡ ማለት "ለጊዜው ከሌሎች ጋር ተዳብለው የሚኖሩ፣ ነገር ግን በቀጣይነት በዚያ የመኖር ዋስትና ወይም ዘላቂ መኖሪያ የማግኘት ተስፋ የሌላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ይህም ሰዎቹ ከዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከጎረቤቶቻቸው \ወይም ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ከማያውቋቸው ሰዎች ጋር እንደሚኖሩ ይገልጻል፡፡**



> **በማኅበራዊ ድኅማ ላይ መሆን፣ ወይም በመሠረቱ ቤት አልባ መሆን፣ ምንም ማጣቀሻ ምስክሮች የለህም. . . እናም አብዛኞቹ አከራዮች እንደዚህ ዓይነቱን ሰው መቀበል አይወዱም...የ [የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ወር ኪራይ] የለኝም ... በሁለተኛ ደረጃ፣ የእኔ ቀለም ነው ችግሩ፣ አንዳንድ አከራዮች እንደዚህ ዓይነት ሰው አይወዱም። አንድ ጊዜ ወደ አንዲት ሴት ሄጄ ነበር፣ ስጠይቃት ከጥቁር ሰዎች ጋር ችግር እንዳላት ተናግራኛለች።**

የካናዳ “ቀይ-መስመር”: በዘር የተለዩ ቡድኖች ብዙውን ጊዜ ደህንነቱ ያልተጠበቀ፣ ጤናማ ያልሆነ፣ ዝቅተኛ ደረጃ ያለ እና ከፍተኛ የወንጀል መጠን ባላቸውና ለአነስተኛ አማካይ ገቢ የተመደቡትን መኖሪያ ቤቶች እንዲቀበሉ ይገደዳሉ።

**ስዉር ቤት-አልባነት**: ከሚታዩት ቤት-አልባዎች በተጨማሪ ከ450,000 - 900,000 የሚደርሱ ካናዳውያን “ድብቅ” ቤት አልባዎችን ይወክላሉ።
**ዘር**: ወደ ቤት እጦት ሊያመሩ የሚችሉ ቁልፍ ሰበቦች ድህነት እና “አናሳ ዘር መሆን” ናቸው።
በዘር የተለዩ ሰዎች የሚገጥማቸው የቤት እጦት በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ በከፍተኛ ደረጃ ያለ ሲሆን፣ እንዲሁም ለማይረቡ መኖሪያ ቤቶች የመዳረግ ዕድል ያጋጥሟቸዋል።
በኦንታሪዮ ውስጥ የሚኖሩ መጤ ሰፋሪዎች እና ስደተኞች በድህነት፣ በአድልዎ፣ በማህበራዊ ፕሮግራሞች መቆረጥ፣ በቤት አገልግሎቶች እጥረት፣ እና ስለ መብቶቻቸው በቂ መረጃ ባለማግኘት ምክንያት ለመኖሪያ ቤት-አልባነት አደጋ የተጋለጡ ናቸው።



በ2017 በኦንታሪዮ ውስጥ የአንድ መኝታ ቤት አፓርታማ አማካይ ኪራይ $ 994 ነበር። ይህ ኪራይ ተመጣጣኝ እንዲሆን ለአንድ ሰው በሰዓት የሚከፈለው ደሞዝ $19 እንዲሆን ያስፈልጋል።



ቶሮንቶ ውስጥ ለአንድ አፓርታማ መኝታ ቤት አማካይ ኪራይ እ.ኤ.አ. በ 2016 $ 1,132 ነበር። አንድ ሰው ይህንን ኪራይ ለመክፈል ብቁ መሆን የሚችለው ደሞዙ በሰዓት (ከገቢ 30% ወይም ከዛ በታች) $ 21.77 መሆን ይኖርበታል ማለት ነው።

## ፈጣን ማስታወሻዎች

ስለ ባለ ቀለም ህዝቦች ስንነጋገር የዘር መሠረታችውና ቅሬተ-ቅርሳቸው ከአውሮፓ ያልሆኑትን ካናዳውያንን ማለታችን ነው። እነዚህም ካናዳ ውስጥ የተወለዱና ከካናዳ ውጭ የትም የተወለዱ፣ በሁለቱም ጎራ ስላሉ የቀለም ሰዎች መናገራችን ነው።
ነባር የአገሬው ተወላጆች ስንል በአገሪቱ የነበሩ ቀድምት ህዝቦች {First Nations / Natives} [የተመዘገቡና እውቅና የተሰጣቸው እንዲሁም ያልተመዘገቡ) ሜቲስ እና ኢንዩት ስለሚባሉ ሕዝቦች ነው።
በቶሮንቶ ውስጥ በድህነት ከሚኖሩት ሰዎች ውስጥ 62% የሚሆኑቱ በዘር ልዩነት ከሚታዩ ቡድኖች የመጡ ናቸው።
በካናዳም በዘር ልዩነት ከሚታዩት ውስጥ 52% የሚኖሩት በኦንታሪዮ ውስጥ ነው።

በካናዳ ውስጥ በዝቅተኛ ገቢ ተቆራጭ (LICO) ወይም በዝቅተኛ የገቢ ልኬት (LIM) የሚመደቡ ቤተሰቦች ከገቢዎቻቸው ውስጥ በጣም ከመቶኛ ውስጥ ትልቁን የሚያጠፉት በአስፈላጊና መሠረታዊ ነገሮች ማለትም እንደ ምግብ እና መጠለያ የመሳሰሉት ናቸው። ድህነትን የምንለካውም በዚህ መንገድ ነው።
**ስልታዊ ዘረኝነት** ብዙዉን በስውር በሚሠራ ተቋማዊና የተዛባ ፖሊሲ፣ ልምምድና አሠራር ምክንያት የሚፈጸም ሆኖ በተለያዩ ቡድኖች መካከል አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ አሠራር ነው።
የተወሰኑ ቡድኖችን በተለያዩ መንገዶች እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል አስቀድሞ ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ ሁልጊዜም እንደተለመደው አካሄድ ብቻ የመከተል ውጤት ሊሆን ይችላል።



አነስተኛ የደመወዝ ጭማሪ ቢደረግ እንኳን ገቢአቸው በሰዓት $19 ዶላር የሆነ ሰዎች ኪራይ የመክፈል አቅማቸው አነስተኛ ስለሚሆን የሚፈልጉትን ቤት ላያገኙ ይችላሉ።

የኦንታሪዮ መንግሥት እ.ኤ.አ. ግንቦት 2017 ባደረገው የደሞዝ ማሻሻያ አዋጅ እንቅስቃሴ እ.ኤ.አ. ከጥር 2019. አነስተኛ ደመወዝ በሰዓት ወደ $15 ከፍ እንዲል ጥሪ አቅርበዋል።
ይህንን ጭማሪ ተግባራዊ ማድረግ በዘር መለየት ምክንያት የተጎዱትን ማኅበረሶቦች ደህና መኖሪያ ቤት የማግኘት አቅም እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል።

# ምን እየተደረገ ነው?

**ዜሃአውኖግ ጋሚክ፣ ኒሽናውቤ** ቤቶች የተባሉ ድርጅቶች ለት/ቤት ወይም ለሥራ ዕድል ወደ ቶሮንቶ ለሚመጡት ነጠላ የአገሬው ተወላጅ ዜጎች አቅርቦት አላቸው።

የኒሽነወቤ ቤቶች ከማህበረሰቡ ጋር የሚያገናኙ፣ የቀዳሚ ኗሪ ሕዝቦች (First Nations) ባህልን የሚያንፀባርቁና ለአቅም የሚመጥኑ ቤቶችን ያቀርባሉ።
nishnawbehomes@rogers.com

**ለኦንታሪዮ ተከራይ ነዋሪዎች ለማዕከል ተሟጋች** (ACTO)
በመኖሪያ ቤቶች ጉዳይ ለሰብአዊ መብቶች እና ለፍትህ መሻሻል - አነስተኛ ገቢ ላላቸው ኦንታሪዮያውያን በህግ ማማከር እና በውክልና፣ ሕግን በማሻሻል፣ ማህበረሰብን በማደራጀት፣ ስልጠናን እና ትምህርትን በመስጠት ይሠራል።
www.acto.ca